በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-200816

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ልማት ፋና የደን ማሕበር

ተጠሪ፡- የአቶ አበበ ወልደየስ ሚስትና ወራሾች

1) ወ/ሮ ብዙዬ ደጀኔ
2) ወ/ሮ አረጋሽ አበበ
3) ወ/ሮ ፀሐይ አበበ
4) አቶ ተመስገን አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጠሪዎች አባት የተከሉትን ባሕር ዛፍ ከሕግ ውጪ ቆርጦ ወስዷል የተባለወን አመልካች የባህር ዛፉን ግምት ለማስከፈል የቀረበ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሆኖ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጀመረው ክርክር የአሁን ተጠሪዎች ከሣሽ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 6ቀን 2008ዓ/ም በተፃፈ ክሳቸው በደሴ ከተማ ቧንቧ ውሐ ክፍለ ከተማ ሚች አባታቸው በሊዝ የመሬት ስሪት ስርዓት ይዘው ለከተማ ግብርና ከሚጠቀሙበት 1035 ካሬ ሜትር ስፋት ካለው ይዞታቸው አዋሣኝ የሆነው መሬት ላይ ወደ ደሴ ከተማ የሚገባውን ናዳ ለመከላከል በአካባቢው ማሕበረሰብ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተሣትፎ ባሕር ዛፍ እንዲተክልበት ከደሴ ከተማ አስተዳደር ከተወሰነ በኋላ ማህበረሰቡ ለመትክል ፈቃደኛ ባመለመሆኑ የተጠሪዎች አውራሽ እንዲተክሉበት ተፈቅዶላቸው ብቻቸውን ተክለው ያሣደጉትንና በማህበራዊ ፍርድ ቤትም የተረጋጠላቸውን ባሕር ዛፍ አመልካች ምንም መብት ሣይኖረው 500 አውራጅ፣ 800 ማገር 350 ቋሚ 3000 ጠርዝ በአጠቃላይ ግምቱ 94,000.00 የሚያወጣውን ባሕር ዛፍ ሰኔ 1ቀን 2001ዓ/ም ቆርጦ የተጠቀመበት መሆኑን በመዘርዘር ግምቱን ከልዩ ልዩ ወጪ ጋር እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች መሬቱ የመንግስት በመሆኑ ተጠሪዎች ክስ የማቅረብ መብት የሌላቸው መሆኑን፤ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት ከውል ውጪ በመሆኑ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው ማለፍንና ግምቱም የተጋነነ መሆኑን፣ ጉዳዩ አስተዳደራዊ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ክሱን በቀጥታ የማዬት ስልጣን የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አመልካች ማሕበር በመሆኑ ከከተማ አስተዳሩ 34,000 ካሬ ሜትር መሬት ለከተማ ግብርናና ለደን ልማት ተሰጥቶት ከ1994ዓ/ም ጀምሮ ባሕር ዛፍ አልምቶ እየተጠቀመ የሚገኝ እንጅ የተጠሪን ባሕር ዛፍ ቆርጦ አለመውሰዱን በከተማው እና በተጠሪ ይዞታ ላይ ይደርስ የነበረውን ናዳ እየተከላከለ ያለው ባሕር ዛፍ አመልካች የተከለው መሆኑን ለተጠሪም ባሕር ዛፍ እንዲተክሉ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆኑን በመዘርዘር የተጠሪ ክስ ውድቅ እንዲሆንለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ ካደረገ በኋላ የተጠሪዎች አውራሽ በመንግስት ቦታ ላይ ባሕር ዛፍ እንዲያለሙ ተፈቅዶላቸው አልምተው ነበር ወይስ አልነበረም? አልምተው ነበር ከተባለስ አመልካች ቆጥሮ ወስዷል ወይስ አልወሰደም? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት ይዞ የግራቀኙ ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች እና ጉዳዩ የሚመለከተው የክፍለ ከተማው የመንግስት አካል ስለጉዳዩ አጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ የቀረበለትን ማስረጃ መርምሮ የተጠሪዎች አውራሽ ባህር ዛፍ ተክየበታለሁ የሚሉት መሬት የመንግስት መሆኑንና እንዲተክሉበት ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ አላረጋጡም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ባህር ዛፍ የተጠሪዎች አውራሽ መትከላቸው በተረጋጠበት ባሕር ዛፉን እንዲተክሉ ፈቃድ አልተሰጣቸውም በሚል ያቀረቡት ክስ ውድቅ የመደረጉን ተገቢነት በጭብጥነት ይዞ የግራ ቀኙን ክርክርና ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ የቀረበለትን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የከተማው ምክር ቤት ለተጠሪዎች አባት ፈቅዶላቸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ባሕር ዛፍ መትከላቸውን አመልካችም የራሱን ባሕር ዛፍ ሲቆርጥ የተጠሪዎች አባት የተከሉትን ባሕር ዛፍ ደርቦ መቁረጡ አረጋግጫለሁ በሚል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ በባለሙያ የተገመተውን 27,977.60 ብር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ተብሎ ፀንቷል፡፡

ይህ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚለው አመልካች ጥር 4ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ፣ የተጠሪዎች አውራሽ

ከሚመለከተው የመንግስት አካል ተፈቅዶላቸው ባህር ዛፍ መትከላቸውና ባሕር ዛፉን አመልካች የቆረጠባቸው ስለመሆኑ ሣይረጋገጥ የባህር ዛፍ ግምትና ወጪና ኪሣራ እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረም ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር እንዲመረመር ተጠሪዎችም የመልስ ክርክር እንዲያቀርቡ በታዘዙት መሰረት የመልስ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ተጠሪዎች በበኩላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወሰነው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር ውሣኔው እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር መልስ መልስ አቅርበው የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡ እንደተመረመረው ለክርክሩ መነሻ የሆነው የተጠሪዎች አውራሽ ጉዳዩ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ባገኙት ፈቃድ መሰረት በመንግስት ይዞታ ላይ ተክለው ተንከባክበው ያሣደጉትን ባሕር ዛፍ አዋሣኝ የሆነው ተጠሪ የራሱን ባሕር ዛፍ ሲቆርጥ የእነሱን ጨምሮ የቆረጠባቸው መሆኑን በመዘርዘር ግምቱን እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በመንግስት ፈቃድ ባሕር ዛፍ አለመትከላቸውን እሱም ቆርጦ አለመውሰዱን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

የተካደ ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራት የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች በመንግስት ይዞታ ላይ ባሕር ዛፍ እንዲተክል የፈቀደለት የክፍለ ከተማው ሕዝብ ለመትከል ፈቃደኛ ሣይሆን ሲቀር የተጠሪዎች አውራሽ እንዲተክሉበት የተፈቀደላቸውና ተክለው ሲንከባከቡ የነበረ ስለመሆኑ፣ ካደገ በኋላም ለመቁረጥ እንዲፈቀድላቸው ጉዳዩ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ጥያቄ አቅርበው ለጊዜው ለመቁረጥ ያልደረሰ መሆኑን የተገለፀላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም የተጠሪዎች አባት የተከሉትን ባሕር ዛፍ ጨምሮ በመቁረጥ የወሰደ ስለመሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም ከተሰጠው ይዞታ በላይ መያዙ በቦታው ከአመልካች በፊት የተጠሪዎች አባት ባህር ዛፍ ተክለው ሲንከባከቡ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ ይህን ማስረጃ የመዘነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባህር ዛፉን በባለሙያ እንዲገመት ተደርጎ የባህር ዛፉን ግምትና ወጪና ኪሣራ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

እንዲሚታወቀው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) እንደሚደነግገው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የመጨረሻ ውሣኔ በተሰጣባቸው ጉዳዮች የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተትን ማረም መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በዚህ መሰረት በያዝነው ጉዳይ እንዲጣራ የተፈለገው የማስረጃ ምዘና መርህን ሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የቀረቡት ማስረጃዎች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር አንፃር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተገኘ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

## ውሣኔ

1) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 0104428 በሆነው ጥቅምት 24ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-30550 ታሕሳስ 9ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2) ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የዬራሣቸውን ይቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

1. ይህ ችሎት የካቲት 5ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ እልባት ያገኘ በመሆኑ ተዘግቷል፣

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም